EthioLion

# እግርኳስ በአምስተርዳም

ከበልጅግ አሊ
-፩-

ዘመን አልፎ ዘመን ሲለወጥ ብዙ ሁኔታዎች ይለወጣሉ ። የሚኒስከርትና ፋሽን ተቃውሞ የተማሪውን ንቅናቄ እንዳላስፋፋት ዛሬ ደግሞ ፋሽን ኢትዮጵያዊነትን ለማጉላት ፣ አንድነትን ለመግለጽ መጠቀሚያ ሆኗል ። የፋሽን ማሳየት ከነበሩት ዝግጅቶች አንዱ ነበር ። እንደው ከፋሽን ልጀምር ብዬ ነው እንጂ የአውሮፓ ስምንተኛው የኢትዮጵያውያን የእግርኳስ ውድድር ኢትዮጵያውነትን አጉልቶ በማሳየት በተሳካ ሁኔታ ተፈጽሟል ።ይህንን ዝግጅት ለመመለከት ከየአገሩ የመጡት ኢትዮጵያውያን ብዙ ነበሩ

በተሳካ ሁኔታ ተፈፅሟል በምልበት ጊዜ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ላይሆን ይችላል ። ለእኔ ተሳካ የምለውን በተደጋጋሚ በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ዝግጅቶችን ወያኔ በገንዘብ ብዛት እየደለለ ለራሱ ፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ሲያደርጋቸው እንደነበር የሚታወቅ ነው ። የአምስተርዳሙ ዝግጅት ግን ኢትዮጵያዊነት ጎልቶ የታየበት ፣ የወያኔ ካድሬዎች የተሸማቀቁበት ፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተውለበለበበት ( የወያኔ ሰማያዊ ድሪቶ ሳይጨመር ) ስለ አንድነት የተዘፈነበት ፣ የሌላ ሃገር ዜጎች ሳይቀሩ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ የሆነ ልብስ እየለበሱ ሲዘዋወሩ የታየበት ስለሆነ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በእስፖርቱም አንፃር ወጣቶች የተወዳደሩበት ፣ ሲያሸንፉ የዘፈኑበት ፣ ሲሸነፉ የተናደዱበት ፣ በዘፈን ግጥም የተሰዳደቡበት ፣ እልኩም ፣ ቁጣውም ፣ ስድቡም የታየበት ነው ። ከጨዋታውም በኋላ ተቃቅፈው ኢትዮጵያ .. ኢትዮጵያ እያሉ የዘፈኑበት ነበር ።

በበኩሌ የዚህን ዝግጅት አዘጋጅ ኮሚቴ ልናመሰግነው ይገባል ባይ ነኝ ።ዝግጅቱ ያማረ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ። መቼም ይህ ጎደለ ፣ ይህ አልተደረገም የሚል ትችት ይነሳ ይሆናል ። ትችቱ ጥሩ ነው ለሚቀጥለው ዝግጅት ትምህርት ይሆናል ። ቢሆንም ግን ይህ ዝግጅት ምን ያህል አድካሚ እንደሆነ ደግሞ የምንረዳው ነው ። እኔ ከኮሚቴው ያየሁት ችግር ብዙ አይደለም ። ገና የመጀመሪያው ዝግጅቱ ለሆነውና ልምድ ለሌለው ኮሚቴ ስህተት አይኑር ማለት የማይሆን ነው ። ያም ሆኖ ምንም የጎላ ስህተት አልተመለከትኩም ። በዝግጅቱ ላይ ስህተት ነው ተብሎ ሲነገር የሰማሁት ለምሳሌ ለምን በትልቅ ሜዳ አልተዘጋጀም ፣ አዳራሹ ጠበበ ፣ የመኪና ማቆሚያ ትንሽ ነው ፣ ዘፈኑ የወጣቶች ብቻ ሆነ ፣ እኔ የምወደው ሙዚቃ አልተዘፈነም ፣ ስለዚህም ባህላችን ገደል ገባ . . . . እንደዚህ ዓይነት የቅንጦት ትችቶች ነበሩ ።አምስተርዳምን ጠንቅቀን ለምናውቀው የቦታን ጥበት በተመለከተ እነዚህ ትችቶች ተገቢ እንዳልሆነ እንረዳዋለን።ሙዚቃውም ቢሆን ማንን አስደስቶ ማንን ለማስከፋት የተደረገ ነው ተብሎ ማማት ይቻላል? ለመሆኑ የተዘፈኑት ሙዚቃዎች ከጉራማይሌነታቸው የተነሳ በምን ቋንቋ እንደሆነ ለማወቅ የሚችግር አይደለም ? ከሁሉም ያስደሰተኝ የወላይተኛው ዘፈን ነበር ።

እኔ ያየሁት ድክመት የተመልካቹ ነው ።የስፖርት ሜዳ ለስፖርት ነው ። በእዚህ ቦታ ሊደረጉ የሚገባቸውና የማይገባቸው ተግባሮች አሉ ። ቢደረጉ እንኳ በድብቅ መሆን የነበረበት ብዙ ስህተቶችን ተመልክቻለሁ ። ለምሳሌ የአዘጋጅ ኮሚቴው ከልክሎት የነበረው ጫት መቃም፣ ሲሻ ማጨስ በአደባባይ ሲደረግ ነበር ። ሲሻ ከባድ ነገር እንዳልሆነ አንዳንዶች ያነጋገርኳቸው ነግረውኛል ። ግን ሕፃናት በተሰበሰቡበት ቦታ ፣ አደባባይ ላይ ማጨስ አስነዋሪ ነው ። ጫትም እንደዚሁ ። ብዙዎቹ መኪና ውስጥ ተደብቀው የሚቅሙ ሲኖሩ አንዳንዱ ግን ግልጽ ፣አደባባይ ላይ፣ ባልተደበቀ ሁኔታ ሕፃናት በሚመለከቱበት ያንን ማድረግ ልንቆጠብበት የሚገባ ነው ። እነዚህ ስህተቶች ደግሞ የኮሚቴው ናቸው ማለት አንችልም ።ኮሚቴው ከኛው የተውጣጣ ስለሆነ እኛ ያወጣውን ሕግ ካላከበርንለት ምን ማድረግ ይችላል? ጫቱም ሆነ ሲሻው ከጀርባ ሆነው ንግዱን የሚጧጡፉት የወያኔ ሰዎች መሆናቸውን የምናውቀው ነው ።ሃገሩ ስትነካ ቱግ ብሎ የተነሳው ወጣት በገንዘቡ ጠላትን እያከበረ መሆኑን መረዳት ያስፈልገዋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የተመለከትኩትና የታዘብኩት የተለያዩ ዝግጅቶች በምሽት በከተማው ውስጥ መካሄዳቸው ነው ።ይህ አሁንም በወያኔ ሰዎች ከበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ በስተጀርባ የተዘጋጀ መሆኑን ለመገመት አያዳግትም ። ኮሚቴው ለፍቶ ያዘጋጀው ዝግጅት እያለ በየቦታው ሌሎች መዘጋጀታቸው በቀጥታ ይህንን ኮሚቴ ለማክሰር የሚደረግ ጥረት ሆኖ ነው ያገኘሁት ። ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ዓይነት ሴራዎችን ወደፊት በሚዘጋጁት ዝግጅቶች ላይ ማክሸፍ ይኖርብናል ።

EthioLion



በተለይ ከሁሉም የሚያስደስተው የተለያዩ የባሕል ዕቃዎች ሲሸጡ የተመለከትኩት ነው ።ለአውሮፓውያን ስጦታ ለመስጠት የምናስብ በሙሉ የሃገራችን የባሕል ዕቃዎች ጥሩ አማራጭ ይሆናሉ ። መጽሕፍት በሰፊው የሚሸጡበትም ዝግጅት ነበር ።

ወደፊት የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም በእንደዚህ ዓይነት ቦታ እየተገኙ ዓላማቸውን ቢያስተዋውቁ መልካም ነው ። ሁሉም ፖለቲከኞች ይፈቱ፣ ብርቱካን ትፈታ  የሚል ካርድ  በአንድነት ዩኬ  እና የኢትዮጵያ ፓለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ሲያሠራጩ ነበር ።ኢሣት የቴሌቪዥን ፕሮግራም እርዳታ ሲሰበስብ ታይቷል ።የዓለም አቀፍ ሴቶች ድርጅትም በአንድ አባላቸው የተለያዩ ወረቀቶችን ሲበተኑ እንደነበር ተመልክቻለሁ። ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችም ሌላው ቢቀር በጽሁፍ እንኳ ዓላማቸውን እንዲያሰራጩ ይገባል ።ይህ ማለት ደግሞ አንዱ የፖለቲካ ድርጅት  ሌላውን የሚሰድብበት፣ የሚያንቋሽሽበት ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ፣ አንድነትን ሊጎለብት የሚችል መሆን ይኖርበታል ። እንደዚህ ቁጥሩ የበዛ ኢትዮጵያዊ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ወያኔ በፖለቲካው ሠርጎ እንዳይገባ የአንድነት ሃይሎች ቦታውን ሊሞሉት ይገባል ።

የወያኔ ደጋፊዎች የወያኔን ፕሮፖጋንዳ ማሰራጨቱ ላይ አደገኝነቱ የታየ ነው ። በወያኔ ግፍ ልቡ የቆሰለው ሁሉ ይህችን አንድ ኢትዮጵያውያን ሊገናኙበት የሚችሉበት መንገድ ለመዝጋት ወያኔ የሚያደርገውን ጥረት እሺ ብሎ እንደማይቀበለው በዚህ ዝግጅት ተመስክሯል ። የወያኔ ባንዲራ ፣ የወያኔ ማልያ ፣ የወያኔ መከፋፈያ መንገድ ሁሉ ተቀባይነት አይኖራቸውም ።አደጋም አላቸው። ወያኔዎችም ይህንን ማወቅ ሊዘነጋቸው አይገባም ። አምስተርዳም ኢትዮጵያዊነትን አጉልቷል ፣ አክብሯል ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን አውለብልቧል ።በሚቀጥለው አመት ለንደን ላይ የሚደረገው ዝግጅት የበለጠ የተሣካ እንደሚሆን በማመን በጉጉት እንጠብቃለን። የኢትዮጵያ ወጣቶች አሁንም እንደገና ለኢትዮጵያዊነት ተሰልፈው የወያኔን ሴራ ያከሽፉበታል የሚል ተስፋ አለኝ ። የወያኔ ባለስልጣናት በውስጥ እርስ በርሳችን በመከፋፈል የሚያደርጉት ሴራም በተደጋጋሚ ሊጋለጥ ይገባል።

ከዚህ በተረፈ ለዘጠነኛው ሎንዶን ላይ ያገናኝን በማለት እሰናበታለሁ ።

ስለኛ የሚያስብ በሰላም ያስብ !

beljig.ali@gmail.com

EthioLion.com